

እውነታዎች:

# ከአካል ጉዳተኞች ጋር ለሚሰሩ ሰራተኞች የመጣው መርሃ-ግብር

ከአካል ጉዳተኞች ጋር ስለሚሰሩ ሰራተኞች የወጣው መርሃ-ግብር ከጁላይ 1 2020 ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል። ይህም የሚከተሉትን ያካትታል

- ቪክቶሪያ ውስጥ ከአካል ጉዳተኞች ጋር ለሚሰሩ ሁሉም ሰራተኞች የወጣ የስነምግባር ደንብ
- አቅራቢዎች እና ከአካል ጉዳተኞች ጋር የሚሰሩ ሰራተኞች የተጠቃሚዎችን ደህነነት አደጋ ላይ ስለሚጥሉ ከአካል ጉዳተኞች ጋር የሚሰሩ ሰራተኞች የሚያውቁ ከሆነ ይህንኑ የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው።
- ቪክቶሪያ ውስጥ በሚገኝ ማንኛውም ከአካል ጉዳተኞች ጋር የሚሰሩ ሰራተኞች በሚያቀርቡት የአገልግሎት ጥራት እና ደህነነት ላይ ቅሬታ ካለ ወደ ገለልተኛ ቅሬታ ተቀባይ አገልግሎት ሪፖርት ማድርግ ይቻላል።

## ሰለ ደንቡ

የስነምግባር ደንቡ የአካል ጉዳተኛ የሆኑ ሰዎችን ከጥቃት እና ከጉዳት ለመከላከል ጠቃሚ መሳሪያ ነው። ይህም የሚደረገው ቪክቶሪያ ውስጥ ያሉ ያልተመዘገቡ ከአካል ጉዳተኞች ጋር በሚሰሩ ሰራተኞች ስራቸውን ሲያከናውኑ ተግባራዊ ሊያደርጉት የሚገባውን ግዴታ በግልጽ በማስቀመጥ ነው። የስነምግባር ደንቡ በሁሉም ከአካል ጉዳተኞች ጋር በሚሰሩ ሰራተኞች ላይ ተፈጻሚ ነው። ይህም በኤንዲአይኤስ ወይንም በሌሎች አቅራቢዎች የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኙትን ያጠቃልላል።

የአካል ጉዳተኛ አገልግሎት ጠባቂ ስነምግባር ደንብ (ደንቡ) በአካል ጉዳተኛ አገልግሎት ጠባቂ መመሪያ 2020 ላየ በግልጽ ተቀምጧል። እነዚህም *የአካል ጉዳተኛ አገልግሎት ጠባቂ ሕግ 2018* (ሕጉ) ውስጥ በዝርዝር የተቀመጡ ሕጎች ናቸው።

ደንቡ ቪክቶሪያ ውስጥ ያሉ ሁሉም ከአካል ጉዳተኞች ጋር የሚሰሩ ሰራተኞች ስራቸውን ሲያከናውኑ በተግባር ሊያደርጉ የሚገባቸውን ግዴታ በግልጽ ያስቀምጣል እንዲሁም የአካል ጉዳተኛ የሆኑ ሰዎችን ከጥቃት እና ከጉዳት ለመከላከል የሚረዱ መመዘኛዎችን እና ደረጃዎችን ያቀርባል።

ደንቡ የተቀረጸው በኤንዲአይኤስ ላይ የተዘረዘሩትን የጥራት እና የጠባቂ ማዕቀፎችን በማጠናከር ቪክቶሪያ ውስጥ ከአካል ጉዳተኞች ጋር የሚሰራ ደህንነቱ የተጠበቀ እና እውቀት ያለው የሰራተኛ ሃይል እንዲኖር ለማድርግ ነው። ደንቡ የኤንዲአይኤስን የስነምግባር ደንብን ይቀበላል፣ ቪክቶሪያ ውስጥ ያሉትን የሰራተኞች ተፈላጊ ብቃት ተመሳሳይ እንዲሆን የተቻለውን ያደርጋል፣ ይህም በኤንዲአይኤስ ወይንም በሌሎች አቅራቢዎች የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኙት ላይ በሙሉ ተፈጻሚ ይሆናል።

### የስነምግባር ደንቡ ማንን ይመለከታል?

ደንቡ ተቀጥረው ወይንም የአካል ጉዳት አገልግሎት ለሚሰጡ ቪክቶሪያ ውስጥ ላሉ በሁሉም ከአካል ጉዳተኞች ጋር ለሚሰሩ ሰራተኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል የገንዘቡ ምንጭ ከምንም ቢሆን።

## ሰለ ማሳወቅ

ከአካል ጉዳተኞች ጋር የሚሰሩ ሰራተኞች ደንበኞቻቸውን ጉዳት ላይ የሚያደርሱ ነገሮችን ሲያደርጉ የተመለከተ ማንኛውም ሰው ይህንን ሊነግረን ይችላል። ይህ ‘ማሳወቅ’ ይባላል። *በአካል ጉዳተኛ አገልግሎት ጠባቂ ሕግ 2018* መሰረት ከአካል ጉዳተኞች ጋር የሚሰሩ ሰራተኞች እና አሰሪዎቻቸው ሰራተኞች ከሚጠበቀው የስራ ባህሪ ውጭ ባህሪ ካሳዩ ይህንኑ ለቪክቶሪያ የአካል ጉዳተኛ ሰራተኞች ኮሚሽን የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው።

ይህ የአካል ጉዳተኛ ሰራተኞች መቆጣጠሪያ መርሃግብር የቪክቶሪያ የአካል ጉዳተኛ ሰራተኞች ኮሚሽን የአካል ጉዳተኛ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎች ላይ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ እንዲያውቅ ያስችለዋል በዚሁም መሰረት የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ላይ በተሻለ መልክ ጉዳት እንዳይደርስ ለመከላከል አና ከጉዳት ለመጠበቀ ያስችለናል። ከአካል ጉዳተኞች ጋር የሚሰሩ ሰራተኞች ወይንም አሰሪዎች ከአካል ጉዳተኞች ጋር የሚሰራ ሰራተኛ ማሳወቅ የሚገባቸውን የባህሪ ግድፈት እንዳሳየ በተገቢ ሁኔታ ካመኑ ይህንን የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው።

# ጠንካራ፣ ደህነነቱ የተጠበቀ የአካል ጉዳተኞች ዘርፍ እንዲመሰረት ያግዙ።



## ቪክቶሪያ ውስጥ ያሉ ከአካል ጉዳተኞች ጋር የሚሰሩ ሰራተኞች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን አሁን የቪክቶሪያ የአካል ጉዳተኛ ሰራተኞች ኮሚሽን ይቀበላል።

የቅሬታ መቀበያ መንገዳችን ገለልተኛ፣ ከተጽዕኖ ነጻ እና ያለክፍያ የሚቀርብ ነው። ስለ እያንዳንዱ ከአካል ጉዳተኞች ጋር የሚሰሩ ሰራተኞች ቅሬታ በሚደርስብን ጊዜ፡ ጉዳዩን የምንይዘው ጥራትን፣ ደህንነትን፣ ቅልጥፍናና እና ዘላቂነትን ለማሻሻል በማለም ነው።

## ከአካል ጉዳተኞች ጋር የሚሰሩ ሰራተኞች ምዝገባ በፈቃደኝነት ከጁላይ 1 2021 ይጀመራል።

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ከአካል ጉዳተኞች ጋር የሚሰሩ ሰራተኞችን በተለያየ መልክ ተጽዕኖ እንዳሳደረባቸው፣ ሃሳብ እና ጭንቀት እንደፈጠረባቸው እንዲሁም በዚሁ የስራ ዘርፍ ላይ እርግጠኛ እንዳይሆኑ እንዳደረጋቸው እንገነዘባለን። ምዝገባውን በ12 ወራት ማራዘም በዚህ ስራ ላይ የተሰማራው የሰው ሃይል ወደ አዲስ ምዝገባ ከመግባቱ በፊት ካለፈ ቀውስ በደንብ ለማገገም ይረዳዋል።

### ሰለ ቪክቶሪያ የአካል ጉዳተኛ ሰራተኞች ኮሚሽን

የቪክቶሪያ የአካል ጉዳተኛ ሰራተኞች ኮሚሽን አዲስ የተቋቋመ ገለልተኛ ወገን ነው። የሚመራው በኮሚሽነሩ ዳን ስታብስ (Dan Stubbs) ሲሆን ዋና ተግባሩም የአካል ጉዳት ያለባቸውን ሰዎች በተሻለ መልኩ ጥበቃ ማድረግ እና ጠንካራ፣ ደህነነቱ የተጠበቀ የአካል ጉዳተኞች ዘርፍ እንዲመሰረት ማገዝ ነው።

የዚህ የስነምግባር ደንብ ዋና ሐላፊነት ከአካል ጉዳተኞች ጋር የሚሰሩ ሰዎች ስራቸውን ለማከናወን ቢያንስ ቢያንስ ማወቅ ያለባቸን ነገር ሁሉም ሰው እንዲያውቀው ማድረግ እና የቅሬታ አገልግሎት መስጠት ናቸው። ኮሚሽኑ ሰለ ጉዳዩ ካወቀ፣ ጉዳዩን የመመርመር ስልጣን አለው እንዲሁም የሰዎችን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ሰራተኞችን ሊያግድ ይችላል።

ድረ ገጻችንን **vdwc.vic.gov.au** ይጎብኙ ወይንም ወደ 1800 497 132 ላይ ይደውሉ
ጋዜጣችንን ለማግኘት እዚህ ይመዝገቡ
ይከታተሉን

vdwc.vic.gov.au
Call 1800 497 132

Victorian Disability Worker Commission

VICTORIA State Government